፫፫. እነርሱም ሃይማኖት የጐደላ ቸው ናቸው፣ ክርስቶስ ከድንግል እንዲወለድ ስለእርሱ በነቢያት የተጻፈውንም ልብ አላደረጉትም፣ እነሆ ድንግል ትፀንሳለች፣ ወንድ ልጅ ንም ትወልዳለች፣ ስሙም አማኑኤል ይባላል፣ ያለውን እየሰሙና እያነበቡ አላወቁም፣ ሕፃን ተወልዶልናልና፣ ወንድ ልጅም ተሰጥቶናልና፣ አለቅ ነትም በጫንቃው ላይ አለ፣ ስሙም ድንቅ መካር፣ የሰላም አለቃ ይባላል፣ እኔ ለአለቆች ሰላምን አመጣለሁና፣ ሕይወትም የእርሱ ነው፣ ገናናነት በፊቱ ነው፣ ለሰላሙም ፍጻሜ የለ ውም ያለውን አላወቁም

፫፬. ፍጻሜ በሌላት ምግባራቸውም ክፋት ስለዚህም አቤቱ ቃላችንን ማን ያምነናል? ክንድህስ ለማን ተገለጠ? አለ ።

፩. ኢሳ. ፯. ፲፬ - ፲፮

፪. ኢሳ. ፱. ፮ - ፯

፲፫. ወካዕበ ይቤ ሰሚዐ ትሰምዑ ወኢትሴብዉ ወራእየ ትሬእዩ ወኢተአምሩ እስመ ጽሉል ልቦሙ ለዝንቱ ሕዝብ።

፲፬. ወበእንተዝ ተሠወረት እምኔሆሙ ጥበብ እስመ ርእዮሙ ኢየ አምሩ ወሰሚዖሙ ኢይሴብዉ።

፲፭. ወአንትሙሰ ሕዝብ በከመ ተውህበ መንግሥት እንዘ ቀዲሙ ኢተአምርዎ ለእግዚአብሔር ወይ እዜሰ አእመርክምዎ በርትዕት ሃይማኖት ወስብከተ ወንጌል ለኢየሱስ ክርስቶስ መድኃኒነ ወሀቤ ሕይወት ለኵሎሙ እለ ይሴፈዉ ኪያሁ።

፲፮. ናሁ አንትሙሰ ጎደግሙ አምልኮ ጣዖታት እለ አልቦሙ ነፍስ ወመ ነንክሙ መሥዋዕተ ርኩሰ ወክሕድ ክምዎሙ ለመኳንንተ ጽልመት።

፲፱. ወበእንተዝ በእክሙ ውስተ ብርሃን ዘበአማን በእግዚእነ ኢየሱስ ክርስቶስ ወቦቱ አእምርክምዎ ለፅ ጻድቅ እግዚአብሔር አብ፤ ወኮንክሙ ወራስያነ መንግሥቱ ለክርስቶስ እስመ ተጠመቅሙ በሞቱ ወበትን ሣኤሁ።

፳. መፍትው ትኩኑ ከመ ሕፃናት እለ ይእዜ ተወልዱ እለ አልቦሙ እከይ ውስተ ልቦሙ።

፲፫. ዳግመኛም መስማትን ትሰማላችሁ አታስተውሉም፣ ማየትን ታያላችሁ አታውቁም አለ፣ የዚህ ሕዝብ ልቡና የደነቆረ ነውና።

፲፬. ስለዚህም ጥበብ ከነርሱ ተሠወረች፣ አይተው አያውቁምና፣ ሰምተውም አያስተውሉምና።

፲፭. እናንተ ሕዝቦች ግን መንግሥተ ሰማያት እንደተሰጣችሁ መጠን ቀድሞ እግዚአብሔርን ሳታውቁት ትኖሩ ነበረ፣ ዛሬ ግን በቀናች ሃይማኖት በወንጌል ትምህርት እርሱን ተስፋ ለሚያደርጉ ሰዎች ሁሉ ሕይወትን የሚሰጥ መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስን አወቃችሁት።

፲፮. እነሆ እናንተስ ነፍስ የሌላ ቸው ጣዖታትን ማምለክን ተዋ ችሁ፣ የጨለማ አበጋዞችን ክዳችሁ ርኩስ መሥዋዕትን ናቃችሁ።

፲፱. ስለዚህም በጌታችን በኢየሱስ ክርስቶስ ወደ እውነተኛው ብርሃን ገባችሁ፣ በርሱም አንድ እውነተኛ እግዚአብሔር አብን አወቃችሁት፣ የክርስቶስ መንግሥተንም ወራሾች ሁናችሁ፣ በሞቱ በትንሣኤው ተጠ ምቃችኋልና።

፳. በልቡናቸው ክፋት እንደሌላቸው ዛሬ እንደተወለዱ ሕፃናት ትሆኑ ዘንድ አገባብ ነው።

፲፭. አዕትቱ እምኔክሙ ኃጢአተ እስመ በዘወክሙ በደሙ ክቡር ከመ ታምልክዎ ለእግዚአብሔር ሕያው።

፲፮. ይቤ እግዚአብሔር በውእቱ መዋዕል በእንቲ አስራኤል በጎበ እለ ኢየአምኑ ትትሀየድ እምኔ ሆሙ መንግሥተ ሰማያት ወትት ወሀብ ለሕዝብ እለ ይገብሩ ጽድቀ።

፲፫. ወአንትሙሰ ቅንኡ እዝኪረ ፍሬ ጥዑም ጥበብ እስመ ኪያክሙ ፈነወ ትካት ጎበ ዐጸደ ወይን።

፲፬. ወእሙንቱሰ ኢይሰምዕዎሙ እስመ አግዘፉ ልቦሙ።

፲፭. ውቱንሥኡ ላዕለ ዐቀብተ ወይኑ ለእግዚአብሔር ወአጎዝዎሙ ቦ ዘቀ ተሉ ወቦ ዘወገሩ በዕብን፣ ወቦ ዘቀ ተሉ በሰይፍ፣ ወቦ ዘወሠሩ በሞ ሠርት፣ ወቦ ዘቀተሉ በውስተ ቤተ መቅደስ ።

፲፮. ወዓዲቀተልዎ ለወራሲ ወመ ነንዎ ለዕብን እንተ መነንዎ ነደ ቅት ።

፲፯. ወበእንቲኣክሙ ይቤ ሕዝብ ዘኢ የአምር ተቀንየ ሊተ ወበውስተ ምስ ማዐ ዕዝን ተሰጥዉኒ።

፲፰. ኃጢአትንም ከናንተ አርቁ፣ ሕያው እግዚአብሔርን ታመልኩት ዘንድ በከበረ ደሙ አድኗችኋልና።

፲፱. እግዚአብሔር ስለ እስራኤል በዚያ ወራት እንዲህ አለ፣ ባላመኑ ሰዎች ዘንድ መንግሥተ ሰማያት ከነርሱ ተለይታ ጽድቅን ለሚሠሩ ሰዎች ትሰጣለች አለ።

፳. እናንተ ግን ደስ የሚያሰኝ የዕ ውቀት ፍሬን ለማድረግ መንፈሳዊ ቅንዓትን ቅኑ፣ እናንተን ቀድሞ ወደ ወይን ቦታ ልኳልና።

፳፩. እነርሱ ግን አይሰሟቸውም፣ ልቡ ናቸውን አደንድነዋልና።

፳፪. የእግዚአብሔርን ወይን በሚ ጠብቁ ላይ ተነሣስተው ይዘው የገደሉት አለ፣ በድንጋይ የወገሩት አለ፣ በሰይፍ የገደሉት አለ፣ በመ ጋዝ የተረተሩት አለ፣ በቤተ መቅ ደስ ውስጥ የገደሉትም አለ።

፳፫. ዳግመኛም ወራሹን ገደሉት አናጢዎች የናቁት ድንጊያንም ናቁት።

፳፬. ስለናንተም ፈንታ የማያውቀኝ ሕዝብ ተገዛልኝ፣ በጀሮ መስማያ ውስጥ መስሉልኝ አለ።

አንቀጽ ፴

በእንተ ከመ መፍትው ንለቡ ክር ስቲያን ገቢረ ዕለተ ፋሲካ ወኢን ስሐት ገቢረ በካልዕ መዋዕል ዘእን በለ በሰሙን በዘቦቱ ይከውን ፍሥሕ አመ ፲ወ፬ ለሠርቀ ሌሊት።

፩. መፍትው ለክሙ አ ፍቁራን አኃው ዘተሣየጠክሙ በደሙ ክቡር ክርስቶስ ትግበሩ በዓለ ቀድስት ፋሲካ በኵሉ ጥንቃቄ ወልቡና ::

፪. እስመ ይዔሪ መዓልት ወሌሊት አመ ፲ወ፭ ለወርኀ መጋቢት።

፫. ጠይቁ እንከ ሐሳበ እስመ ኢሐመ እግዚእነ በአሐቲ ዓመት ፪ተ ጊዜ፣ ወአንትሙኒ ተዓቀቡ ትግበሩ ተዝካረ ሕማማቲሁ አሐተ ጊዜ በዓመት፣ እስመ በእንቲአነ ሞተ ::

፬. ወኢትጎበሩ ገቢረ በዓል ምስለ አይሁድ እስመ አልቦ ፍቅር ማዕ ከሌነ ወማዕከሌሆሙ እስመ እሙ ንቱ ስሕቱ በዕበደ አእምሮ ሐሳብ እንዘ ይመስሎሙ ዘይፈጽሙ።

፭. ወበእንተዝ ኮኑ እሠራነ በዲበ ምድር ወውፅኣነ እምጽድቅ።

ሠላሳኛ አንቀጽ

ክርስቲያን የፋሲካ በዓል የሚደ ረግበትን ዕለት ማስተዋል እንደሚ ገባ ይናገራል፣ በዐሥራ አራተኛው ሌሊት ፋሲካ ኦሪት በሚሆንበት በሰሙነ ሕማማት ነው እንጂ በሌላ ቀን በማድረግ እንዳንስት እናስተ ውል ዘንድ እንዲገባ ይናገራል።

፩. ክርስቶስ በከበረ ደሙ የዋጃችሁ የተወደዳችሁ ወንድሞች ሆይ! የቅድ ስት ፋሲካን በዓል በፍጹም መረዳትና ማስተዋል ታደርጉ ዘንድ ለእናንተ አገባብ ነው።

፪. በመጋቢት ወር በ፲፭ኛው ቀን መዓልትና ሌሊት ይተካከላልና።

፫. እንግዲህ ቍጥርን ተረዱ፣ ጌታ ችን በአንዲት ዓመት ሁለት ጊዜ አልታመመምና፣ እናንተም የሕማ ማቱን መታሰቢያ በዓመት አንድ ጊዜ ታደርጉ ዘንድ ተጠንቀቁ፣ ስለ እኛ ሙቷልና ::

፬. ከአይሁድም ጋር በዓልን አታ ድርጉ፣ በእኛና በእነርሱ መካከል ፍቅር የለምና፣ እነርሱ የሚፈጽሙ እየመሰላቸው የቍጥር ዕውቀትን በስንፍና ስተዋል።

፭. ስለዚህም በምድር ላይ የታሠሩ ከጽድቅም የወጡ ሆኑ ::

፮. ወአንትሙሰ ዕቀቡ ሐሳበ ዕለት አመ ፷ወ፩ ለወርኀ መጋቢት በሐሳ ቦሙ ለዕብራውያን።

፯. ወዕቀቡ ዘንተ ሐሳበ እስከ ፷ወ፭ ለሠርቀ ሌሊት ።

፰. ወዓዲ ኢትስሐቱ ሐሳበ ፍሥሕ ከመ ኢይኩን ቅድመ ሆሣዕና ወኢይኩን ፋሲካ ፪ ጊዜ በአሐቲ ዓመት በኢጠይቆ ሐሳብ፤ ዳዕሙ ይኩን ዕለተ ትንሣኤሁ ቅድስት ለእግዚእነ ወአምላክነ ወመድኃኒነ ኢየሱስ ክርስቶስ በሰንበተ ክርስቲያን ቅድስት።

፱. ወዓዲ ይኩን ጾመ ቅድስት ፋሲካ እምሰኑይ እስከ ቀዳሚት ሰንበት መሐትወ ፋሲካ።

፲. ወበሰሙነ ሕማማት ኢትብልዑ ወኢምንተኒ ዘእበለ ጎብስት ወሜው ወማይ ።

፲፩. ተዐቀቡ በዝንቱ መዋዕለ አጽዋም እምበሊዐ ሥጋ ወሰትየ ወይን እስመ መዋዕለ ላህ ወንዘን እማንቱ፤ ወፈድፋደሰ በእሉ ሰዱስ ዕለታት።

፲፪. ወእመሰበ ዘይክል ጸዊመ ይትገ ኀሥ ፪ ዕለተ ወእመሰ ኢይክል ይጹም በበሐቲ ዕለት ።

፯. እናንተ ግን በዕብራውያን አቈጣጠር የመጋቢት ወር ሃያ አምስት ተኛ ቀን ቍጥርን ጠብቁ።

፰. ይህን ቁጥር እስከ ሃያ አንደኛው ሠርቀ ሌሊት ድረስ ጠብቁ።

፱. ዳግመኛም የፍስሕን አቈጣጣር አታሳስቱ፤ ከሆሣዕና አስቀድሞ እንዳይሆን፤ ፋሲካም ቍጥርን ባለመ ጠንቀቅ በአንድ ዓመት ሁለት ጊዜ እንዳይሆን፤ የጌታችን የአምላካችንና የመድኃኒታችን የኢየሱስ ክርስቶስ ቅድስት ትንሣኤ በተቀደሰች የክርስቲያን ሰንበት ይሁን እንጂ ።

፲. ዳግመኛም የተቀደሰች የፋሲካ ጾም ከሰኞ እስከ ዋዜማዋ ቀዳሚት ሰንበት (ቀዳም ስዑር ይሁን)።

፲፩. በሕማማት ሳምንትም በጨው ከተሠራ ቂጣና ከውሀ በቀር ምንም አትብሉ አትጠጡ

፲፪. በዚህ የጾም ወራት ሥጋ ከመ ብላት ጠጅ ከመጠጣት ተጠበቁ፤ የልቅሶና የኀዘን ቀኖች ናቸውና፤ ይልቁንም እኒህን ስድስቱን ቀኖች።

፲፫. መጾም የሚቻለው ሰው ቢኖር ሁለት ቀን ይታገሥ፤ ባይችል ግን በየአንዳንዱ ቀን ይጹም ።

፲፫. ወይትዓቀብ እምገቢረ እኩይ እስመ ይቤ እግዚእነ ኢይክሉ ደቂቁ ለመርዓዊ ጸዊመ አምጣነ ሀሎ ምስሌሆሙ መርዓዊ ወባሕቱ ይመጽእ መዋዕል አመ ይነሥእዎ ለመርዓዊ እምኔሆሙ ውእተ አሚረ ይጸውሙ።[፩]

፲፬. እስመ በዝንቱ መዋዕል ሰዱስ ነሥእዎ አይሁድ ለእግዚእነ እምኔነ ወሰቀልዎ ዲበ መስቀል ወጎ ለቍዎ ምስለ ጊጉያን።

፲፭. ወበእንተዝ ንኤዝዘክሙ ትጹሙ ከመ ገበርነ ንሕነ እምድኅረ ዐርገ ውስተ ሰማይ ወባዕዳነሂ መዋዕለ ይጹሙ ረቡዕ ወዓርበ እስከ ተሱዓት ሰዓት ።

፲፮. ወእመቦ ዘያፈቅር ይጹም እስከ የዐርብ ፀሐይ።

፲፯. ወዕቀቡ ሰዓተ ሌሊት እስከ ይነቁ ዶርሆ ተጋቢአክሙ እንከ ውስተ ቤተ ክርስቲያን በስብሐት ወበጸሎት እንዘ ታነብቡ ኦሪተ ወነቢያተ ወመዝሙረ ዳዊት።

፲፰. ወእምድኅረ አጥመቅሙ አን ብቡ ወንጌለ በፍርሀት ወበረዓድ ወመሀርዎሙ ለሕዝብ በቀዳሄተ ወመድኀኒተ ነፍሶሙ።

፲፱. ክፉ ሥራ ከመሥራትም ይጠ በቅ፣ ጌታችን የሙሽራ ሚዜዎች ሙሽራው ከእነርሱ ጋራ ሳለ መጾም አይችሉም፣ ነገር ግን ሙሽራውን ከነርሱ የሚወስዱበት ጊዜ ይመ ጣል ፣ ያን ጊዜ ይጾማሉ እንጂ ብሏልና።

፳. በዚህ በስድስተኛው ቀን አይሁድ ጌታን ከኛ ወሰዱት፣ በመስቀል ላይም ሰቀሉት፣ ከበደለኞችም ጋራ ቈጥረውታልና ።

፳፩. ስለዚህም እኛ እንደሠራነው ትጾሙ ዘንድ እናዛችኋለን፣ ወደ ሰማይ ካረገ በኋላ ሌሎችንም ቀኖች ረቡዕንና ዓርብን እስከ ዘጠኝ ሰዓት ይጹሙ ።

፳፪. ፀሐይ እስኪገባ ሊጾም የሚወድ ሰው ቢኖር ይጹም።

፳፫. ከእንግዲህ በኋላ በቤተ ክርስቲ ያን ተሰብሰባችሁ በምስጋና በጸሎት አሪትንና ነቢያትን፣ የዳዊትንም መዝ ሙር እያነበባችሁ የሌሊቱን ሰዓት ዶሮ እስኪ ጮህ ድረስ ጠብቁ ።

፳፬. ካጠመቃችሁም በኋላ በፍር ሃትና በመንቀጥቀጥ ሁናችሁ ወን ጌልን አንብቡ፣ ለሕዝቡም የሚጠ ቅመውንና የነፍሳቸውን መድኃ ኒት አስተምሯቸው።

፩. ማቴ. ፱ ፡ ፲፭

፲፱. ወሰአልም ለእግዚአብሔር ከመ ይትመየጥ እስራኤል ውስተ ንስሓ ወይድኀን እምዕልወት እስመ መኰንን ተሐፅበ እደዊሁ በማይ፣ ወይቤ ንጹሕ አነ እም ደሙ ለዝ ብእሲ ጻድቅ።

፳. ወእስራኤልሰ ከልሑ ወይቤሉ ደሙ ላዕሌነ ወላዕለ ውሉድነ።

፳፩. ወእምዝ ይቤሎሙ ጲላጦስ እስቅሎኑ ለንጉሥክሙ።

፳፪. ወአውሥኡ ወይቤሉ አልብነ ንጉሥ ዘእንበለ ቄሣር ስቅሉ ስቅሎ፤ እስመ ኵሉ ዘያነግሥ ርእሶ ዐላዌ ነጋሢ ውእቱ።[፪]

፳፫. ወአውሥኡ ወይቤሉ እመአስሕ የውኅ ለዝንቱ ኢኮንክ ዐርኮ ለቄሣር።

፳፬. ወእምዝ ጲላጦስ መኰንን ወሄሮድስ ንጉሥ አዘዙ ይስቅልዎ ከመ ይትፈጸም ዘጽሑፍ ዘይቤ ለምንት አንገለጉ አሕዛብ ወሕዝብ ኂ ነበቡ ከንቶ ወተንሥኡ ነገሥተ ምድር ወመላእክትኒ ተጋብኡ ምስ ሌሆሙ ኀቡረ ላዕለ እግዚአብሔር ወላዕለ መሲሑ፤[፫] ወካዕበ ይቤ ወገደፉ እኁዋሆሙ ከመ በድን ርኩስ።

፲፱. እስራኤልም ወደ ንስሐ ይመለስና ከክህደት ይድን ዘንድ እግዚአብሔርን ለምኑት፣ ፈራጁ ጲላጦስ እኔ ከዚህ ጻድቅ ሰው ደም ንጹሕ ነኝ ብሎ እጆቹን ታጥቧልና።

፳. እስራኤል ግን ደሙ በኛ ላይና በልጆቻችን ላይ ይሁን ብለው ጮሁ።

፳፩. ከዚህ በኋላ ጲላጦስ ንጉሣችሁን ልስቀለውን አላቸው።

፳፪. እነርሱም ያለ ቄሣር ንጉሥ የለንምና ስቀለው ስቀለው ብለው መለሱ፣ ራሱን ንጉሥ የሚያደርግ ሁሉ የንጉሥ ከዳተኛ ነውና።

፳፫. ይህን ብታድነው የቄሣር ወዳጅ አይደለህም ብለው መለሱ።

፳፬. ከዚህም በኋላ ንጉሥ ሄሮድስና መስፍኑ ጲላጦስ ይሰቅሉት ዘንድ አዘዙ፣ "አሕዛብ ለምን ዶሉ? ሕዝቡስ ከንቱን ለምን ተናገሩ? የምድር ነገሥታትስ ለምን ተነሡ? አለቆችስ ከእነርሱ ጋራ ለምን ተሰበሰቡ? በእግዚአብሔርና በመሲሑ ላይ ለምን ተሰበሰቡ ? ሁለተኛም ወንድማቸውን እንደ ርኩስ በድን ጣሉ" አለ ተብሎ የተጻፈው ይፈጸም ዘንድ።

፪. ዮሐ. ፲፱ ፡ ፲፪–፲፭

፫. መዝ. ፪ ፩–፪

፭፫. ወእምዝ ሰቀልዎ በዓርብ ወተንሥአ በሣልስት ዕለት፤ ተፈጸመ ዘይቤ መጽሐፍ ተንሥአ እግዚኦ ወኮንኖ ለምድር እስመ አንተ ትወርስ በዙሉ አሕዛብ።

፭፮. ወዓዲ ይቤ ይእዜ እትነሣእ ይቤ እግዚአብሔር እፈሲ መድኀኒተ ወአግህድ ቦቱ ።[፬]

፭፯. ወካዕበ ይቤ ተንሥአ እግዚኦ በመዓትከ ወተሰዐል መልዕልቶሙ ለጸላእትከ[፭] ወዐዲ ይቤ ፍድዮሙ ፍዳሆሙ ላዕለ ርእሶሙ።

፭፰. ወበእንተዝ አንትሙኒ አብኡ ቍርባነክሙ በስመ አዘዘክሙ።

፭፱. እስመ ይቤ ከመዝ ግበሩ ተዝካርየ ጹሙኬ ጸመ በፍሥሓ ወበንሤት ወግበሩ በዓለ እስመ ተንሥአ እግዚእነ ኢየሱስ ክርስቶስ እሙታን ወአስፈወነ ትንሣኤሁ።

፷. ወዛቲ ሥርዐት ሕገ ትኩንክሙ ዘለዓለም እስከ ይመጽእ ዳግመ በስብሐት እስመ አይሁድሰ ኢያ ምኑ ትንሣኤሁ ለመድኀኒነ ወንሕ ነሰ ክርስቲያን ነአምን ትንሣኤሁ እስመ ኵሎሙ ዘይሴፈዉ ትንሣ ኤሁ ቅድስተ ይረክቡ ሕይወተ ዘለዓለም።

፬. መዝ. ፺፩ ፡ ፮

፭. መዝ. ፯ ፡ ፯

፷፩. ከዚህ በኋላም ዓርብ ቀን ሰቀ ሉት፣ ተሰቅሎ በሞተ በሦስተኛው ቀን ተነሣ፣ መጽሐፍ አቤቱ «ተነሥ ተህ ምድርን ግዛት፣ አንተ አሕዛብን ሁሉ ትወርሳለህና» ያለው ተፈጸመ።

፷፪. ዳግመኛም እግዚአብሔር ዛሬ ተነሥቼ መድኃኒትነትን እደርጋ ለሁ እገለጽበታለሁም አለ።

፷፫. ሁለተኛም አቤቱ በቀኣህ ተነሥ፣ በጠላቶችህም ላይ ከፍ ከፍ በል አለ፣ ዳግመኛም ፍዳቸውን በራሳቸው ላይ አምጣባቸው አለ።

፷፬. ስለዚህም እናንተ እንዳዘዛችሁ ቍርባናችሁን አስገቡ።

፷፭. መታሰቢያየን አድርጉ ብሏ ልና፣ ጾምንም በደስታና በሐሤት ጹሙ ፣ ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ከሙታን ተለይቶ ተንሥቶአልና፣ ትንሣኤውንም ተስፋ አድርጎል ናልና፣ በዓልን አድርጉ።

፷. ይህችም ሥርዓት ዳግመኛ በጌት ነት እስኪመጣ ድረስ ለዘለዓለሙ ሕግ ትሁናችሁ፣ አይሁድ የመድ ኃኒታችንን ትንሣኤ አላመኑምና፣ እኛ ክርስቲያኖች ግን ትንሣኤውን እናምናለን፣ ቅድስት ትንሣኤውን የሚያምኑ ሁሉ የዘለዓለም ሕይወ ትን ያገኛሉና።

፴፩. ግበሩ እንከ በዓለ ሰሙነ ዕለተ እስመ እግዚእነ ቦቱ አስተርአየ ለነ፣ ይቤ ቶማስ ሊተኒ አስተርአየኒ ወአስተፍሥሐኒ ቅንዋተ እደዊሁ ወእገሪሁ ወርግዘተ ገቦሁ ቅድስት[1] እዝ ቀዲሙ እናፍቅ ወኢየአምን ትንሣኤሁ አርአየኒ ገሀደ ርግዘተ ገቦሁ ዘየማን።

፴፪. ወበ፴ዓ ዕለት ግበሩ በዓለ እስመ ባቲ ፈጸመ ኵሎ ሥርዓተ ወዐርገ ሰማያተ ኀበ አብ ዘአንሥአ ወነበረ በየማነ ኀይል ወአግረረ ጸላእቶ ታሕተ እገሪሁ ።

፴፫. ወይመጽእ ዳግመ በስብሐት ወበዐቢይ ክብር ይኰንን ሕያዋነ ወሙታነ ወይፈድዮ ለኵሉ በከመ ምግባሩ።

፴፬. ወናሁ ይሬእይዎ ለፍቁር ወልደ እግዚአብሔር ዘሰቀልዎ አይሁድ[2] እስመ አይሁድ ጉቡኣን እዝ ያነብቡ ሰቆቃወ ኤርምያስ ነቢይ ።

፴፭. አመ ፲ ለታስዕ ወርኀ[3] እስመ ለመንፈሰ ሕይወትነ ኢየሱስ ክርስቶስ ነሥእዎ እምኔነ ወአሕመምዎ።

፴፮. እንግዲህ ስምንት ቀን በዓል አድርጉ፣ ጌታችን ለእኛ ተገልጦአል ና፣ ቶማስም አለ ፣ ለእኔ የእጆቹንና የእግሮቹን ችንካሮች የቅድስት ጐኑን መወጋትም አሳየኝ፣ አስቀድሜ እጠራጠርና ትንሣኤውን ሳላምን ሳለሁ የቀኝ ጐኑን መወጋት ገልጦ አሳየኝ፣ ደስም አሰኘኝ።

፴፯. በዐርባኛው ቀንም በዓልን አድርጉ ሥርዓትን ሁሉ ፈጽሞባታልና ወደ አስነሣው እግዚአብሔር አብ ወደ ሰማያትም ዓርጓልና ጠላቶቹንም ከእግሮቹ በታች አስገዛለት።

፴፰. ዳግመኛም በሕያዋንና በሙታን ይፈርድ ዘንድ በታላቅ ክብርና ጌትነት ይመጣልና፣ ለሁሉም እንደእየ ሥራው ይከፍለዋል።

፴፱. ያን ጊዜም እነሆ የሰቀሉት አይሁድ የተወደደ የእግዚአብሔርን ልጅ ያዩታል፣ አይሁድም በዘጠኝኛው ወር በአሥረኛው ቀን የነቢዩ የኤርምያስን የልቅሶ መጽሐፍ እያነበቡ የተሰበሰቡ ናቸው።

፵. የሕይወታችን መገኛ ኢየሱስ ክርስቶስን ከእኛ ወስደው መከራን አጸንተውበታልና ።

፩. የሐ. ፳ ፡ ፲፯
፪. ማር. ፲፩ ፡ ፶፪
፫. ሰቆ. ኤር. ፬ ፡ ፳

፴፮. ወዓዲ ያንብቡ ዘጸሐፈ ባሮክ እንዘ ይብል ውእቱ አምላክነ ወአ ልቦ ባዕድ ዘይትማሰሎ ኪያሁ ወው እቱ ረከበ ለዝሉ ፍኖተ ሕይወት ወወ ሀቦ ለያዕቆብ ገብሩ ወለእስራኤል ፍቁሩ ወአምድኅረዝ ዲበ ምድር አስተርአየ ወአንሶሰወ ከመ ሰብእ።[፱]

፴፯. ወአንቢቦሙ ዘንተ ይበክዩ ወይላህዉ ላሐ ወከመዝ ይገብሩ እንዘ ይሬእዩ መዝበረ ዘገብረ ናቡከደነፆር እንዘ ያመክንዩ ከመ ጥዩቅ ውእቱ።

፴፰. ወአምድኅረ ዐሡር መዋዕል እምዝ ዐርገ፤ ተፍጻሜተ ጸንጠፅስጤ ግበሩ በዓለ።

፴፱. እስመ በይእቲ ዕለት አመ ሣ ልስ ሰዓት ፈነወ ለነ ጸራቅሊጦስሃ ኢየሱስ ክርስቶስ ወመልአ ላዕሌነ ኃይሉ ወተናገርነ በሐዲስ ልሳን፤ ከመ ውእቱ ኢየሱስ ክርስቶስ መሲሑ ለእግዚአብሔር ዘቦቱ ሥልጣን ይኰንን ሕያዋነ ወሙታን።[፲]

፵. ወበእንተዝ ስምዐ ኮነ ሙሴ ወይቤ ከመ እግዚአብሔር አምላክነ ነሥአ እሳተ ወእዝነመ።[፲፩]

፵፩. ወከማሁ ርእዮ ያዕቆብ በአም ሳለ ብእሲ ወይቤ ርኢክዎ ለእግዚ አብሔር አምላክነ ገጸ በገጽ ወድ ኅነት ነፍስየ ።[፲፪]

፵፪. ዳግመኛም ባሮክ «እርሱን የሚ መስለው ሌላ የለምና አምላካችን ነው፤ እርሱም የሕይወትን መንገድ ሁሉ አገኘ፤ ለአገልጋዩ ያዕቆብ ለወዳጁ እስራኤልም ሰጠው፤ ከዚህም በኋላ በምድር ተገለጠ፤ እንደ ሰውም ተመላለሰ» ሲል የጻፈውን ያነብባሉ።

፵፫. ይህንንም አንብበው ያለቅሳሉ፤ ይንሰቀሰቃሉ፤ ናቡከደነፆርም ያደረገውን ፍራሽ አይተው የተረዳ እንደ ሆነ እያመካኙ እንደዚህ ያደርጋሉ።

፵፬. ከዓረገም በኋላ በአስረኛው ቀን በዓለ ሃምሳ ሲፈጸም በዓልን አድርጉ።

፵፭. በዚች ቀን በሦስት ሰዓት ኢየ ሱስ ክርስቶስ ጸራቅሊጦስን ልኮልና ልና፤ በላያችንም ኃይልን መላ፤ ኢየ ሱስ ክርስቶስ የእግዚአብሔር ልጅ በሕያዋንና በሙታን ይፈርድ ዘንድ ሥልጣን ያለው እንደሆነ በአዲስ ቋንቋ ተናገርነ።

፵፮. ስለዚህም ነገር ሙሴ ፈጣሪያችን እግዚአብሔር እሳትን አንሥቶ እንዳዘነመ ምስክር ሆኖ ተናገረ።

፵፯. እንደዚሁም ያዕቆብ በሰው አም ሳል አየው «እንዲህም አለ ፈጣሪያ ችን እግዚአብሔርን ፊት ለፊት አየሁት ሰውነቴም ዳነች» ።

፱. ባሮክ ፫ ፡ ፴፮–፴፯
፲. የሐ. ሥራ ፪ ፡ ፬ ፡ ፲ ፡ ፵፪
፲፩. ዘፍ. ፲፱ ፡ ፳፬
፲፪. ዘፍ. ፴፪ ፡ ፴

፴፪. ወአብርሃምኒ ተወክፎ ከመ ነግድ ወአምነ ከመ ውእቱ ግዚአብሔር፤[15] ገውኣቱ ዘርእዮ ኢያሱ ወልደ ነዌ መኰንን ላዕለ ሠራዊተ ኃይላተ እግዚአብሔር።

፴፫. ወዓዲ ጽኑዕ ውእቱ በንዋየ ሐቅሉ ወረድኦ በኢያሪኮ ወእምዝ ሰገደ ሎቱ ኢያሱ ከመ ዘይሰግድ ገብር ለእግዚኡ።[16]

፴፬. ወካዕበ ዝውእቱ ዘእመሮ ሳሙኤል ነቢይ ከመ ውእቱ ክር ስቶስ መሢሑ ለእግዚአብሔር[17] ወዓዲ ይሰምይዎ ካህናት ወነገሥት መሲሐ።

፴፭. ወዓዲ ውእቱ ዘእመሮ ዳዊት ወይቤ በፍርሀት ከመ ስብሐተ ፍቁር ጕሥዐ ልብየ ቃለ ሠናየ ወአነ አየድዕ ግብርየ ለንጉሥ ከመ ቀለመ ጸሓፊ ዘጠበጠ ይጽሕፍ ልሳንየ ይሜኒ ላህዩ እምውሉደ እመሕያው።

፴፮. ተክዕወ ሞገስ እምከናፍሪከ በእንተዝ ባረከከ እግዚአብሔር ለዓለም።

፴፯. ቅንት ለይፈክ ኀያል ውስተ ሐቌከ በስንከ ወበላህይከ አርትዕ ተሠራህ ወንገሥ በእንተ ጽድቅ ወርትዕ ወየዋሃት።

፴፰. አብርሃምም እንደ እንግዳ ተቀበለው እግዚአብሔርም እንደሆነ አመነ፣ ይኸውም በእግዚአብሔር ሠራዊት ላይ አለቃ የሆነ የነዌ ልጅ ኢያሱ ያየው ነው።

፴፱. ዳግመኛም በጦር መሣርያ የጸና ነበር፣ በኢያሪኮም የረዳው ከዚህም በኋላ ኢያሱ ባርያ ለጌታው እንደ ሚሰግድ ሰገደለት።

፵. ሁለተኛም ነቢዩ ሳሙኤል የእግዚአብሔር መሲሕ ክርስቶስ እንደ ሆነ ያመለከተው ይህ ነው፣ ዳግመኛም ካህናትና ነገሥታት መሲሕ ነው ይሉታል።

፵፩. ዳግመኛም ዳዊት ያመለከተው አውቆት ነው፤ በፍርሃትም እንደ ወዳጅ ምስጋና እንዲህ አለ፣ ልቡናየ በጎ ነገርን አውጥቶ ተናገረ፣ ግብሬንም ለንጉሥ እነግራለሁ፣ አንደበቴም እንደ አማረ ጸሓፊ ቀለም ይጽፋል፣ መልኩም ከሰው ልጅነት ይልቅ ያምራል።

፵፪. ከከንፈሮችህ ባለሟልነት ፈሰሰ፣ ስለዚህም እግዚአብሔር ለዘለዓለሙ መረቀህ።

፵፫. ኃይለኛ ሆይ በደም ግባትህና በመልክህ ላህይ ሰይፍህን በወገብህ ታጠቅ፣ ስለ ጽድቅና ስለ ቅንነት ስለ የዋህነትም ተከናውነህ ንገሥ።

---

15. ዘፍ. ፲፭ ፡ ፩-፲፯
16. ኢያ. ፭ ፡ ፲፫-፲፭
17. ፩ኛ ሳሙ. ፲፪ ፡ ፭

፴፰፤ወይመርሐክ ስብሐተ የማንክ፣ አሕዛክ ስሑል ኃያል፣ አሕዛብ ይወድቁ ታሕቴክ፤ ውስተ ልቦሙ ለጸላእተ ንጉሥ::

፴፱፤ መንበርክ እግዚኦ ለዓለመ ዓለም በትረ ጽድቅ ወበትረ መንግሥትክ፤ አፍቀርክ ጽድቀ ወፀመጣ ጸላእክ::

፵፤ በእንተዝ ቀብዐክ እግዚአብሔር አምላክክ ቅብዐ ትፍሥሕት እም እለ ከማክ[፲፯]::

፵፩፤ወበእንተዝ ይቤ ሰሎሞን እግዚአብሔር ፈጠረኒ ቀዳሜ ፍናቱ ለምግባሩ እምቅድመ ዓለም ሣረረኒ መቅድመ ዘኢንበለ ምድረ ይሜርር ወዘእንበለ ቀላያተ ይግበር ወዘእንበለ ይፃኡ አንቅዕተ ማያት::

፵፪፤ወዘእንበለ አድባር ይጠዐጥዐ እምቅድመ ኩሉ አውግር ወለደኒ[፲፱] ::

፵፫፤ወዓዲ ይቤ ኢሳይያስ ነቢይ ትወጽእ በትር እምሥርወ ዕሤይ ወየዐርግ ጽጌ እምጕንዱ ወይሠየም መኰንን አሕዛብ[፳]::

[፲፯] መዝ ፵፬ : ፯- ፰
[፲፰] ምሳ. ፰. ፳፪. ፳፫
[፲፱] ኢሳ. ፲፩. ፩. ፲

፴፰፤የቀኝህ ጌትነትም ይመራሃል፣ ኃያል ሆይ ጦሮችህ የተሳሉ ናቸው፣ አሕዛብ በበታችህ ይወድቃሉ፣ በንጉሥ ጠላቶች ልብ ውስጥ ::

፴፱፤አቤቱ ዙፋንህ ለዘለዓለም ነው፣የመንግሥትህ ሥልጣን የእውነት ሥልጣን ነውና፣ እውነትን ወደድህ ፣ሐሰትን ግን ጠላህ::

፵፤ስለዚህም እግዚአብሔር አምላክ እንዳንተ ያሉት ምእመናን ከሚቀበሉት ልጅነት የበለጠ ደስ የሚያሰኝ ተዋሕዶን አዋሐደህ::

፵፩፤ስለዚህም ነገር ሰሎሞን እንዲህ አለ፣ እግዚአብሔር ለሥራ መንገድ መጀመሪያ አደረገኝ ፣ ከዓለም አስቀድሞ ምድርን ሳይ ፈጥር ሠራኝ፣ ጥልቆችንም ሳይሠራ የውሀዎች ምንጮችም ሳይወጡ ከዓለሙ ሁሉ አስቀድሞ ሠራኝ ::

፵፪፤ተራሮች ሳይከናወኑ ከኮረብቶችም አስቀድሞ ወለደኝ፤

፵፫፤ ዳግመኛም ነቢዩ ኢሳይያስ «ከሥር ከሆሄይ ሥር ትወጣለች፣ ፍሬም ከግንዱ ይወጣል፣ የአሕዛብ ገዥም ሆኖ ይሾማል»አለ::

፶፬፤ ወካዕበ ይቤ ሰሎሞን ጥበብ ሐነጸት ላቲ ቤተ[፲፱] ::

፶፭፤ወዓዲ ይቤ ዘካርያስ ተፈ ሥሒ ፈድፋደ ወለተ ጽዮን ወስብኪ ወለተ ኢየሩሳሌም ናሁ ይመጽእ ንጉሥኪ ጻድቅ ወመድ ኀን ወየዋህ ውእቱ ወይጼዐን ዲበ አድግ ወዲበ ዕዋለ አድግ[፳]::

፶፮፤ ወዓዲ ይቤ ዳንኤል ውእቱ ወልደ እጓለ እመሕያው በጽሐ እስከ ብሉየ መዋዕል[፳፩] ::

፶፯፤ ውእቱኬ እምደብር ዘወረደ ዕብን ዘእንበለ እድ[፳፪] ወንሕነኒ ዝኬኑ ወንአምነክ ለክሙ ከመ ውእቱ ቃለ እግዚአብሔር ህልው እምቅድመ ዓለም::

፶፰፤ወዓዲ ዕሩይ ውእቱ ምስ ሌሁ በኵሉ ግብር እመኑ ቦቱ ከመ ትርከቡ ሕይወተ ዘለዓ ለም::

፶፱፤ወእመሰ ኢአመንክሞሰ ትረ ክቡ ኵነኔ ወዘሰ ኢየአምን በወ ልድ ኢይሬእያ ለሕይወት ዘለዓ ለም ወመቅሠፍተ እግዚአብሔር ይነብር ላዕሌሁ::

፷፤ሁለተኛም ሰሎሞን ጥበብ ለራሷ ቤትን ሠራች አለ ::

፷፩፤ዳግመኛም ዘካርያስ የጽዮን ልጅ ሆይ! እጅግ ደስ ይበልሽ፤ የኢየሩሳሌምም ልጅ አዋጅን ንገሪ፤እውነተኛ የሚያድን ኃዳጌ በቀል በአህያ ላይና በውርንጫ ዋም ላይ ተቀምጦ ንጉሥሽ ይመጣል አለ ::

፷፪፤ዳግመኛም ዳንኤል የሰው ልጅ እርሱ ከዘመን አስቀድሞ የነበረ ዘመንን አሳልፎ የሚኖር ከመሆን ደረሰ አለ ::

፷፫፤ይኸውም የሰው እጅ ሳይፈነቅለው ከተራራ የወረደ ደንጊያ ነው እኛም ከዓለም አስ ቀድሞ የነበረ የእግዚአብሔር ቃል እንደሆነ ለናንተ እንነግ ራለን እናስተምራለን ::

፷፬፤ ዳግመኛም ከርሱ ጋራ በሥ ራው ሁሉ የተካከለ ነው፤ የዘለዓ ለም ሕይወትን ታገኙ ዘንድ እመ ኑበት::

፷፭፤ባታምኑበት ግን የዘለዓለም ቅጣትን ታገኛላችሁ፤ በወልድ የማያምን ግን የዘለዓለም ሕይወ ትን አያያትም፤የእግዚአብሔርም መቅሰፍት በርሱ ላይ ይኖራል::

፲፱ ምሳ. ፱. ፩
፳ ዘካር፡ ፱- ፱
፳፩ ዳን. ፯ - ፲፫
፳፪ ዳን . ፪. ፴፬ ፡ ፴፭

፮፤ወእምድኅረ በዓለ ሃምሳ ግበሩ በዓለ ስቡዐ ዕለተ ወእምዝ ጹሙ እስመ መፍትው ለነ ንትፈሣሕ ወንትሐሠይ እስመ ከፈለነ ንን ሣእ ጸጋ መንፈስ ቅዱስ ::

፯፩፤ሙሴሰ ወኤልያስ ጾሙ ፵ ዕለተ፤ ወዳንኤልኒ ጸመ ፫ ሰንበ ታተ ወኢበልዐ እክለ ለፍትውቱ ሥጋኒ ወወይን ኢቦአ ወስተ አፉሁ[፴፫]::

፯፪፤ወብፅዕት ሐና ሶበ ለአለቶ ለእግዚአብሔር ይጸግዋ ወልደ፤ ሳሙኤልሃ ትቤ ወይነ ኢስተይኩ ለስኪር አላ ዳዕሙ ጸንዐ ልብየ በእግዚአብሔር[፴፬] ::

፯፫፤ወሰብአ ነነዌ ጸሙ ፫ መዓ ልተ ወ፫ ሌሊተ[፴፭] ::

፯፬፤መርዶክዮስ ወአስቴር በጾም ድኅኑ ወዮዲት በጾም ድኅነት እምሆሎፎርኒስ ዕልው[፴፮] ::

፯፭፤ዳዊትኒ ይቤ ደክመ ብረክየ በጾም ወስሕከ ሥጋየ በኀጢአ ቅብዕ[፴፯] ::

፯፮፤ ወአንትሙኒ ጹሙ ወስአሉ ኀቤሁ ሥርየተ ኃጢአት::

፯፯፤ ወዓዲ ጹሙ ረቡዐ ወዓርበ እዝ ትመጸውቱ ለነዳያን፤ ወአክብሩ ሰንበታተ ተጋቢአክሙ በፍሥሓ ወበሐሤት ውስተ ቤተ ክርስቲ ያን::

፯፰፤ከበዓለ ሃምሳም በኋላ ሰባት ቀን በዓልን አድርጉ፤ ከዚህም ጹሙ፤ ለኛ ፈጽመን ደስ ይለን ዘንድ ይገባናልና፤ የመንፈስ ቅዱስ ሀብትን እንቀበል ዘንድ አድሎና ልና::

፯፱፤ሙሴና ኤልያስም ፵ቀን ጾሙ፤ ዳንኤልም ሦስት ሱባዔ ጸመ፤ ለፍላጎቱም እህል አልበ ላም፤ሥጋና ወይንም በአፉ አል ገባም ::

፹፤ብፅዕት ሐናም ወንድ ልጅ ሳሙኤልን ይሰጣት ዘንድ እግ ዚአብሔርን በለመነችው ጊዜ ወይ ንን ለመስከር አልጠጣሁም ልቡ ናዬ በእግዚአብሔር ጸና እንጂ አለች::

፹፩፤የነነዌ ሰዎችም ሦስት ቀንና ሦስት ሌሊት ጾሙ ::

፹፪፤መርዶክዮስና አስቴርም በጾም ዳኑ፤ ዮዲትም በጾም ከወንጀለኛ ሆሎፎርኒስ እጅ ዳነች::

፹፫፤ ዳዊትም ጉልበቶቼ በጾም ደክሙ ሥጋየም ቅቤን በማጣት ሻከረ አለ ::

፹፬፤እናንተም ጹሙ የኀጢአትንም ሥርየት ከርሱ ዘንድ ለምኑ ::

፹፭፤ዳግመኛም ለነዳያን እየመጸ ወታችሁ ረቡዕንና ዓርብን ጹሙ፤ በቤተ ክርስቲያንም ተሰብስባችሁ በደስታና በሐሤት ሰንበቶችን አክ ብሩ::

፴፫ . ዘመ.፴፱ : ፴፮፤ ዳን.፲- ፪፫
፴፬ . ፩ ሳሙ.፪. ፩
፴፭. ዮና. ፫-፬
፴፮ አስ. ፭. ፴፭ ፵፪
፴፯. መዝ. ፻፰- ፴፱

፳፯፤ወባዕዳነስ ሰንበታተ ኢት ጹሙ ዘእንበለ አሐቲ ዕለት መሐትወ ፋሲካ ::

፳፱፤ወእመሰቦ ዘይጸውም በሰን በተ ክርስቲያን እንተ ይእቲ ትን ሣኤሁ ቅድስት ወጸንጠቀስጤ እስከ በዓለ ፶ ወእለሰ ይንብሩ ከመዝ ወይላህዉ በበዓላተ እግዚ አብሔር አልቦሙ ሥርየተ ኃጢ አቶሙ::

፴፤ ወአንትሙሰ ግበሩ በዓለ መንፈሳዊተ ወግሙራ ኢትረ ስዩ ኀዘነ ውስቴቶን::

አንቀጽ ፴ወ፩

በእንተ ፍልጠተ ዕልዋን ወመናፍቃን ኤጲስ ቆጶሳት::

፩፤ቅድመ ተዐቀቡ እምፍልጠተ ዕልዋን ወመናፍቃን ተገንሡ እምፍኖቶሙ ለርኩሳን ወረኀቁ እምኔሆሙ እስመ ዘይቀርብ ኀቤ ሆሙ ይውሂ በእሳት በላዒ::

፪፤ ኢትሚጡ እንከ ልበክሙ ኀቤሆሙ ወኢትትፈለጡ በበይ ናቲክሙ በአመክንዮ ኦሪአ ሚመት::

፫፤ወእመሰቦ ዘይቀርብ ኀቤሆሙ ወይገብር ምግባሮሙ ይረክብ ኵነኔ ዘለዓለም::

፬፤ለዳታን ወአቤሮን እለ ተቃረ ንዎ ለሙሴ አብቀወት ምድር ወውኀጠቶሙ ወከማሁ ለደቂቀ ቆሬ ፪፻፶ወ፯ እለ ተቃረንዎ ለአ ሮን በልዓቶሙ እሳት፩

፩. ዘኍል ፲፮ - ፴፫

፭፤የፋሲካ ዋዜማ ከምትሆን ከአንዲት ቀን በቀር ሌሎች ሰን በታትን ግን አትጹሙ ::

፮፤ ቅድስት ትንሣኤው በተደ ረገባት በክርስቲያን ሰንበት እና በጰራቅሊጦስ እስከ በዓለ ሃምሳ የሚጸም ቢኖር፣ እንዲህ ለሚያ ደርጉና በእግዚአብሔር በዓላት ቀን ለሚያዝኑ፣ ለኃጢአታቸው ስርየት የላቸውም::

፯፤እናንተ ግን መንፈሳዊ በዓ ልን አድርጉ፣ በነዚህም ውስጥ ፈጽማችሁ ኃዘንን አታድርጉ ::

ሠላሳ አንደኛው አንቀጽ

ከዳተኞችንና የመናፍቃን ኤጲስ ቆጶሳትን ስለመለየት ይናገራል።

፩፤አስቀድማችሁ ከከዳተኞችና ከመ ናፍቃን ስለ መለየት ተጠበቁ፣ ከርኩሳን መንገድ ተለዩ፣ ከእነ ርሱም ራቁ፣ ወደ እነርሱ የሚቀ ርብ በሚባላ እሳት ይቃጠላል ::

፪፤ እንግዲህ ልባችሁን ወደእነ ርሱ አትመልሱ፣ ሹመትን በመ ሻት ምክንያትም እርስ በርሳ ችሁ አትለያዩ::

፫፤ወደ እነርሱ የሚቀርብ ሥራ ቸውንም የሚሠራ ቢኖር የዘለ ዓለም ቅጣት ፍርድን ያገኛል

፬፤ ሙሴን የተቃወሙትን ዳታ ንንና አቤሮንን ምድር ተከፍታ ዋጠቻቸው፤ እንዲሁም አሮ ንን የተቃወሙትን ሁለት መቶ ሃምሳውን የቆሬን ልጆች እሳት በላቻቸው፤የሙሴ እጎት

ወለማርያም እኅተ ሙሴ ሰበ ተዛለፈት ወአውጽዕዋ እምትዕይ ንት ሰቡዕ ዕለተ እመትቤ እፎ ተዓደወ ሙሴ ወአውሰበ ብእሲተ ነኪርተ[፪]::

፩፤ወዓዲ ያዝያን ንጉሠ ይሁዳ አመ ገብረ ግብረ ክህነት ወአዕረገ ዕጣነ ዘኢክነ መፍትው ለገቢር፤ እለ አልዓዛር ካህን ወ፫ ካህናት እለ ምስሌሁ ዘለፍዎ ወዐበየ ሰሚዐ ቃሎሙ ወአስተርአየ ውስተ ገጹ ለምጽ እስመ ተምዖ እግዚአብ ሔር[፫]::

፪፤ወእመሰ ነገሥት እምከመ ተዐ ደዉ ይረክቡ ኵነኔ እፎኬ ፈድፋደ ባዕዳን እለ ይትዐደዉ ላዕለ ካህ ናት እስመ ክህነት ተዐቢ እመን ግሥት::

፫፤ካህናትሰ ይቀንዩ ነፍሳተ ወነገ ሥትኒ ይኬንኑ ሥጋ በመጥባሕት::

፬፤ወእለሰ ይትዐደዉ ላዕለ ካህናት ይትኬነኑ ዐቢየ ኵነኔ እምእለ ይትዐደዉ ላዕለ ነገሥት::

፭፤ወባሕቱ አልቦ ዘይክል ድኂነ እምኵነኔ ክልኤሆሙ::

ማርያም ሙሴ እንዴት ተላለፈ ባዕድ ሴትንስ እንዴት አገባ ብላ ባሸሚጠጠች ጊዜ ሰባት ቀን ከስ ተማ አስወጡአት ::

፩፤ዳግመኛም የይሁዳ ንጉሥ ያዝያን ሊያደርገው የማይገባ ውን የክህነትን ሥራ በሠራና ዕጣን ባሳረገ ጊዜ ካህኑ አል ዓዛርና ከእርሱ ጋር የነበሩ ሰማ ንያ ካህናት መከሩት፤ ቃላቸ ውን መስማትንም እንቢ አለ፤ በፊቱም ለምጽ ወጣበት፤ እግዚ አብሔር ተቆጥቶታልና::

፪፤ነገሥታት ሊደፋፈሩ ቅጣትን የሚያገኙ ከሆነ፤ በካህናት ላይ የሚደፋፈሩ ሌሎችማ እንዴታ ክህነት ከመንግሥት ትበልጣለ ችና::

፫፤ካህናት ነፍሳትን ይገዛሉ፤ ነገ ሥታት ግን ሥጋን በሾተል ይቀ ጣሉና::

፬፤ በካህናት ላይ የሚደፋፈሩ ሰዎች ግን በነገሥት ላይ ከሚ ደፋፈሩ ሰዎች ይልቅ ታላቅ ቅጣትን ይቀጣሉ ::

፭፤ ነገር ግን ከሁለቱም የቅጣት ፍርድ መዳንን የሚችል የለም::

፪ ዘኍ ፲፪ - ፲፭
፫. ፪ኛ ዜና ፳፮ : ፲፯-፳፪

፲፤ወዓዲ ይቤ በእንተ አቤሴሎም ወደቂቀ ቆሬ ወዳታን ወባዕዳንሂ እለ ይትዓደዉ ክህነተ ኢያድኅኑ ርእሶሙ እምኮነኔ እስመ እሉ ተንሥኡ ላዕለ ዳዊት በእንተ መንግሥት።

፲፩፤ወካዕበ ተቃረንዎ ለሙሴ በአፍቅሮ ክዊነ መኰንን ወአቤሴሎም ረሰየ አባሁ መኰንነ ዐመፃ ።

፲፪፤ወካዕበ ይቤ በእንተ ዳታን ወአቢሮን ወአውሥእም ወደቤልዎ ለሙሴ ኢአከለክኑ ዘአውጻእከነ እምብሔረ ግብፅ እምድር እንተ ታውኅዝ ሀሊበ ወመዓረ ወመላህከ አዕይንቲነ ወኮንከ መኰንነ ላዕሌነ[ፀ] ።

፲፫፤ ወእምዝ ተጋብኡ ብዙኃን ወንብሩ ላዕሌሁ ።

፲፬፤ ወከማሁ ደቂቀ ቆሬኒ ይቤሉ ለሙሴኑ ለባሕቲቱ፤ወለአሮን ሊቀ ካህናት ተናገሮሙ እግዚአብሔር ወበንበ ደቂቀ እስራኤልሰ አልቦኑ ንጹሕ ዘእንበለ አሮን ባሕቲቱ።

፲፭፤ወበእንተዝ ዐ ዘይቤሉ ለሙሴ መኑ ሜመከ መልአከ ወመኰንነ ላዕሌነ[ፁ]፤

፲፮፤ስለ አቤሴሎም፤ ስለ ቆሬ ልጆችና ስለ ዳታን ክህነትንም ስለሚደፋፈሩ ስለ ሌሎችም እን ዲህ አለ፤ ራሳቸውን ከቅጣት አያድኑም፤ እነዚህ ስለ መንግሥት በዳዊት ላይ ተነሥተዋልና።

፲፯፤ሁለተኛም ፊሬጅ መሆንን በመውደድ ሙሴን ተቃወሙት፤ አቤሴሎምም አባቱን የዓመፃ ገዥ አደረገው ።

፲፰፤ዳግመኛም ስለ ዳታንና አቤሮን እንዲህ አለ፤ ሙሴን ወተትና ማርን ከምታፈስስ ከግብፅ ምድር ያወጣኸን ዐይኖቻችንንም ማውጣትህ በእኛም ላይ አለቃ መሆንህ አልበቃህምን ብለው መለሱለት»

፲፱፤ከዚህ በኋላ ብዙዎች ሰዎች ተሰብስበው በርሱ ላይ ተባበሩ።

፳፤እንዲሁም የቆሬ ልጆች እግዚአብሔር ሙሴን ብቻውንና የካህናቱን አለቃ አሮንን ተናገራቸውን በእስራኤል ልጆች ዘንድስ ከአሮን ብቻ በቀር ንጹሕ የለምን አሉ ።

፳፩፤ስለዚህም ሙሴን በእኛ ላይ አለቃና ገዥ አድርጎ ማን ሾመህ ያሉ አሉ።

ፀ ዘጎ ፲፮ ፡ ፲፫ - ፲፭
ፁ ዘጎል ፲፮ ፡ ፲፫ ፤ዘጎል ፲፪.፪

፲፮፤ ወእምዝ ተንሥኡ ላዕለ ሙሴ ብእሴ እግዚአብሔር ወምእመን ዘገብረ ኵሎ ተአምራተ፤ ወፈጸመ ኵሎ መንክራተ፤ ወአውረደ ላዕለ ሰብአ ግብጽ ብዙኀ መቅሠፍት፤ ሰጠቀ ማየ ወአቀመ ባሕረ ከመ ዐረፍት እምለፈ።

፲፯፤ ወአውፅአሙ ለሕዝብ እምህየ ከመ ዘየሐውር ውስተ የብስ ፤ ወተ ሰጥመ ፈርዖን ወሠራዊቱ ወኵሉ ጎይሉ ውስተ ባሕር፤ ወአንቅዐ ኵሎሐ ወአውሐዘ ሎሙ ማየ፤ ወወ ሀቦሙ መና እምሰማይ ወአዝነመ ላዕሌሆሙ ሥጋ ከመ መሬት፤ ወመርሖሙ መዓልተ በደመና ወኵሉ ሌሊተ በብርሃነ እሳት[፮]።

፲፰፤ ወዓዲ ወሀቦሙ ሕገ በአፉሁ ለእግዚአብሔር አኃዜ ኵሉ ወፀ ጽላተ ዘዕብን እለ ጽሑፍ ውስቴ ቶን ዐሥሩ ቃላት በአፃብዒሁ ለእግዚአብሔር ወተናገሮ እግዚአ ብሔር ገጸ በገጽ ከመ ይትናገር ብእሲ ምስለ ዐርኩ[፯] ።

፲፱፤ ከዚህ በኋላ የእግዚአብሔር ሰውና ታማኝ በሆነ፣ ታምራ ቱን ሁሉ በአደረገ፣ ድንቅ ሥራ ዎችንም ሁሉ በፈጸመ፣ በግብፅ ሰዎችም ላይ ብዙ መቅሠፍትን ባወረደ፣ ውሀንም ከፍሎ በወ ዲያና በወዲህ እንደ ግድግዳ ባቆመ በሙሴ ላይ ተነሡ።

፳፤ ሕዝቡን ከዚያ በደረቅ እንደ ሚሄድ አወጣቸው፣ ፈርዖንም ከሠራዊቱና ከኃያላኑ ሁሉ ጋራ በባሕሩ ውስጥ ተሰጠመ፣ ጭን ጫውንም ሠንጥቆ ውሀን አፈሰ ሰላቸው፣ መናንም ከሰማይ ሰጣ ቸው፣ ሥጋንም በላያቸው እንደ መሬት አዘነመ፣ ቀን በደመና ሌሊቱንም በእሳት ብርሃን መራ ቸው ።

፳፩፤ ዳግመኛም ሁሉን በፈጠረ እግዚአብሔር ቃል ሕግንና በእግዚአብሔር ጣቶች የተጻፉ ዐሥሩ ቃላት በውስጣቸው የተጻ ፉባቸው ሁለቱን የደንጊያ ጽላ ቶች ሰጣቸው፣ እግዚአብሔ ርም ሰው ከወዳጁ ጋራ እንደ ሚነጋገር ፊት ለፊት ተነጋ ገረው።

፮ ዘፀ. ፲፫ ፲፫-፲፰፤

፯. ዘፀአ ፴፪.፲፩

፲፱፤ወበእንቲአሁ ይቤ ኢይትነሣእ ነቢይ በከመ ሙሴ [፳] ::

፳፤ ወላዕለ ዝንቱ ብእሲ ተንሥኡ ላዕሌሁ ደቂቀ ቆሬ ወሮቤል ወገ ርም በዕብን እንዘ ይጼሊ[፱]::

፳፩፤ወውእቱሰ ይብል ኢትነጽር ዲበ መሥዋዕቶሙ ወቍርባኖሙ ወውጎጠቶሙ ምድር ወእምዝ አስ ተርአየ ስብሐተ እግዚአብሔር::

፳፪፤ወቦ እለ በልዐቶሙ እሳቅ ወከማሁ ለእለ የንሥሡ ሚመተ በዐመፃ ውጎጠቶሙ ምድር ምስለ ተዓይኒሆሙ ወሰሉ ንዋዮሙ ወረዱ ውስተ ሲኦል ሕያዋኒሆሙ[፲]::

፳፫፤ ወእመሰ ለእሉ ፈደዮሙ እግ ዚአብሔር ኮነኔ መቅሠፍት እፎኬ ላዕለ እለ ይተልዉ ፍኖቶሙ ለዕል ዋን ወመናፍቃን ወይፀርፉ ላዕለ ፍጥረተ ግብሩ::

፳፬፤ወአንትሙኒ አ አኃው ስምዑ ቃለ ተግሣጸ መጻሕፍት ወተዐ ቀቡ እምፍልጠተ አእምሮ ወኢ ይኩን ሕፀፀ ሃይማኖትክሙ ::

፲፱፤ ስለ እርሱም እንዲህ አለ፤ እንደ ሙሴ ያለ ነቢይ አይነ ሣም::

፳፤በዚህ ሰው ላይ የቆሬና የሮ ቤል ልጆች ተነሥተው እየጸለየ ላለ በደንጋይ ደበደቡት ::

፳፩፤እርሱም አለ፤ መሥዋዕታቸውን ቍርባናቸውን አትቀበል፤ ምድ ርም ዋጠቻቸው፤ ከዚህም በኋላ የእግዚአብሔር ክብር ተገለጠ ::

፳፪፤እሳት የበላቻቸው አሉ፤ እን ዲሁም ሹመትን በዐመፅ ሲፈ ልጉ ከገንዘባቸው ሁሉና ከስተ ሞቻቸው ጋራ ምድር የዋጠቻ ቸው በሕይወታቸውም ሳሉ ወደ ሲኦል የወረዱ አሉ ::

፳፫፤እግዚአብሔር ለነዚህ የመቅ ሠፍት ፍርድን ከሰፈላቸው የስ ሐዲዎችንና የመናፍቃንን መን ገድ በሚከተሉ ላይና የእጁን ፍጥረት በሚፀርፉ (በሚሰድቡ) ላይማ እንዴት ይሆን?

፳፬፤ወንድሞች ሆይ፤ እናንተም የመጻሕፍትን ምክር ስሙ ከዕ ውቀት ከመለየትም ተጠበቁ፤ ሃይማኖታችሁም ጉዶሎ አይ ሁን ::

፳ ዘዳግ ፲፰፡ ፲፱
፱ ዘጎ ፲፱ : ፲
፲ ዘጎ ፲፯ : ፴፩

፳፭፤ወኢትጎሥሡ ነሚአ ሚመት በጎበ ዕልዋን ወመናፍቃን እለ ያማስንዎሙ ለሕዝብ።

፳፮፤ረጎቁ እምዕልወቶሙ ወኢ ትትአረክዎሙ እስመ ይቤ እግዚ አብሔር ተገጎሡ እምእለ ይገብሩ ከመዝ ከመ ኢትትጎጕሉ ምስ ሌሆሙ[፲፩]።

፳፯፤መፍትው ተፈልጦ እምእለ ይፀ ርፉ ላዕለ ስመ እግዚአብሔር እስመ ነቢር ምስለ ዕልዋን ወመናፍቃን ያርጎቅ እምእግዚአብሔር ወእሙ ንቱ እለ ይትቃረኑ ምስሌሁ ።

፳፰፤ ወበእንተ እስዮሙ ረሡሰት ምድር በስመ ይቤ ኤርምያስ ነቢይ ርጎቁ ዝንቱ ሕዝብ እኩይ እምእግዚአብሔር ሕያው ።

፳፱፤ወካዕበ ይቤ ጎደጉ ቤትየ ወር ስትየ ወሜጥኩ ገጽየ እምኔሆሙ።

፴፤ ወካዕበ ይቤ ለዐፀደ ወይንየ ኢይክርይዋ ወኢይገምድዋ ወኢያ ስተናጽሕዋ አላ ዳዕሙ ይበቍል ውስቴታ ሦክ ወእሜክላ ወኢይ ኤዝዝ እንከ ዲቤሃ ደመና ከመ ይዝንም ዝናም ወትከውን በድው[፲፪]

፴፩፤እስመ እግዚአብሔር ጎደጎሙ ለዝንቱ ሕዝብ ከመ ጽላሎተ ሐይ መት ማዕከለ ዐጸደ ወይን ወከመ ዐቃቤ ዳስ ወከመ ሀገር ምዝብርት[፲፫]።

፲፩ ዘጕ ፲፯ : ፳፫
፲፪. ኢሳ. ፭ . ፮
፲፫ ኢሳ . ፩ . ፰

፳፭፤ሕዝብን በሚያጠፏቸው በመ ናፍቃንና በወንጀለኞችም ዘንድ ሹመት መቀበልን አትፈልጉ።

፳፮፤ ከወንጀልኝነታቸው ራቁ፤ ጓደኞችም አትሁኗቸው፤ እግዚ አብሔር ከእነርሱ ጋራ እንዳት ጠፉ እንዲህ ከሚያደርጉ ሰዎች ተለዩ ብሏልና።

፳፯፤ በእግዚአብሔር ስም ላይ ከሚሳደቡ ሰዎች መለየት አገ ባብ ነው፤ ከክሐዲዎችና ከመና ፍቃን ጋራ መኖር ከእግዚአብ ሔር ያርቃልና እነዚህም ከርሱ ጋራ የሚከራከሩ ናቸው ።

፳፰፤ ስለ ክፋታቸውም ምድር ረከሰች፤ ነቢዩ ኤርምያስ ይህ ክፉ ሕዝብ ከሕያው እግዚአብ ሔር ራቁ እንዳለ ።

፳፱፤ሁለተኛም አለ፤ ቤቴንና ርስ ቴን ተውሁ፤ ፊቴንም ከእነርሱ መለስሁ።

፴፤ዳግመኛም አለ፤ የወይን ቦታ ዬን አይቆፍሯትም፤ አይቆርጧት ምም አያፀዷትም፤ነገር ግን በው ስጧ እሾህና አሜክላ ይበቅላል፤ እንግዲህም ዝናም ይዘንም ዘንድ ደመናን በእርሷ ላይ አላዝም ምድረ በዳም ትሆናለች።

፴፩፤እግዚአብሔር እሊህን ሕዝብ በወይንቦታ መካከል እንዳለ የድ ንኳን ጥላ እንደ ወይን ጠባቂ ዳስ እንደ ፈረሰችም ከተማ ትቷ ቸዋልና።

፴፪፤ ወአሴስል እምኔሆሙ መን ፈስ ቅዱስ መንፈስ ትንቢት።

፴፫፤ ወለዛቲስ ቤተ ክርስቲያን መልዓ አሎቴተ መንፈሳዊተ ከመ ፈለገ ግብጽ ዘበመዋዕለ ክረምት ወአልዓላ ከመ ቤት ዲበ ርእሰ ደብር ጥሉል[፲፩]።

፴፬፤ ደብር ርጉዕ ወደብር ጥሉል ደብር ዘሠምሮ የኀድር እግዚአብሔር ውስቴቱ ወይኅብር ለዓ ለም[፲፪]።

፴፭፤ ወካዕበ ይቤ በኤርምያስ ነቢይ ምግባሩ ለልዑል ስቡሕ ወቅዱስ መካን ድልው ለነ[፲፫]።

፴፮፤ ወዓዲ ይቤ በኢሳይያስ በውእቱ መዋዕል ያስተርኢ ደብረ እግዚአብሔር ዲበ አርእስተ አድባር ነዋኃት ወቤተ እግዚአብሔር ላዕለ ማዕዘንት ወይትሌዓል ፈድፋደ መልዕልተ አውግር[፲፬]።

፴፯፤ ወበእንተዝ ኀደጎሙ እግዚአብሔር ለሕዝበ አይሁድ ወረሰየ ምኵራቦሙ በድወ ወሠጠጠ መንጦ ላዕቶሙ ወነሥአ መንፈስ ቅዱሰ እምኔሆሙ በከመ ጽሑፍ ናሁ ይት ኀደግ ለክሙ ቤትክሙ በድው[፲፭] ።

፴፰፤ ትንቢትን የሚያናግር መን ፈስ ቅዱስንም ከእነርሱ አርቃ ለሁ አለ።

፴፱፤ ይህችን ቤተ ክርስቲያን ግን በክረምት ወራት እንደሚ ሆን እንደ ግብጽ ፈሳሽ መን ፈሳዊ ምስጋናን መላት በለመለመ በተራራ ራስ ላይ እንዳለ ቤትም ከፍ ከፍ አደረ ጋት።

፵፤ የማይናወጽ የለመለመ ተራራ እግዚአብሔር የወደደው በውስጡም እግዚአብሔር አድ ሮበት ለዘለዓለሙ ይኖራል።

፵፩፤ ዳግመኛም ነቢይ ኤርምያስ የልዑል እግዚአብሔር መቀመ ጫው የተመሰገነ ክቡር ንጹሕ ቦታ ለኛ የተዘጋጀ ነው አለ ።

፵፪፤ ዳግመኛም በኢሳይያስ እን ዲህ አለ «በዚያ ወራት የእግዚ አብሔር ተራራ በረጃጅም ተራ ሮች ራሶች ላይ፤ የእግዚአ ብሔርም ቤት በማዕዘናት ላይ ይታያል፤ በኮረብቶችም ላይ ፈጽሞ ከፍ ከፍ ይላል።››

፵፫፤ ስለዚህም እግዚአብሔር የአ ይሁድ ወገኖችን ተዋቸው፤ ምኵ ራባቸውንም ምድረ በዳ አደረገ፤ መጋረጃቸውንም ቀደደ፤ ቤታ ችሁ እነሆ ምድረ በዳን ይሆናል ተብሎ እንደ ተጻፈ መንፈስ ቅዱስን ከነርሱ አራቀ ።

፲፩ ሲራክ ፲፬ ፡ ፳፫
፲፪. መዝ. ፷፯. ፲፮
፲፫ ኤርም ፲፯. ፲፪
፲፬ ኢሳ ፪. ፪
፲፭. ማቴ. ፳፫. ፴፰

፴፯፤ ለክሙሰ ሕዝበ ክርስቲያን ተውህበ ለክሙ አኰቴተ መንፈስ ቅዱስ በከመ ጸሐፍ በኢዩኤል ነቢይ እሠውጥ መንፈስየ ዲበ ኵሉ ዘሥጋ ወይትኔበዩ ደቂቅ ክሙ ወአዋልዲክሙ ወመራዙቲክሙ ራእየ ይሬእዩ ወሊቃውንቲክሙ ሕልመ የሐልሙ[፲፱]። እስመ ኀይለ ጥበብ ወአእምሮ አሰሰለ እግዚአ ብሔር እምአይሁድ ወወሀበክሙ ለክሙ።

፴፰፤ ወበእንተዝ ቀንአ ዲያብሎስ ላዕለ ቅድስት ቤተ ክርስቲያን ዘእ ግዚአብሔር ወአምጽአ ላዕሌክሙ ፍርሀተ ወረዓደ ሕማመ ወምንዳቤ ወኵሉ ፅርፈተ።

፴፱፤ ወፍልጠትሰ እምኀበ ዕልዋን እስመ ሰይጣን ቀነዮሙ ለሕዝበ አይሁድ ከመ ይቅትሉ ክርስቶ ስሃ።

፵፤ ወአንትሙሰ ጸላዕክምዎሙ ወመነንክሙ እከየ ምግባሮሙ ወበ እንተዝ አምጽአ ላዕሌክሙ መን ሱተ ወጽልአ በከመ ገብረ ላዕለ ጻድቅ ኢዮብ[፳]።

፵፩፤ ወበከመ ተቃረኖ ለኢያሱ ወልደ ኢዮሴዴቅ[፳፩]። ወለነኒ ብዙኀ ጊዜ ያተ ይፈቀድ ሰይጣን የሐንፍጸነ ከመ ዐለንስ ወከመ ያድክም ሃይማኖተነ[፳፪]።

፵፪፤ የክርስቲያን ወኖች ሆይ! ለእ ናንተ ግን የመንፈስ ቅዱስ ምስጋና ተሰጣችሁ፤ በነቢዩ ኢዩኤል መን ፈሴን በሥጋዊ ሁሉ ላይ አሳድ ራለሁ፤ ወንዶችና ሴቶች ልጆ ቻችሁም ትንቢትን ይናገራሉ፤ ጉልማሶቻችሁም ራዕይን ያያሉ፤ ሽማግሌዎቻችሁም ሕልምን ያል ማሉ፤ ተብሎ እንደ ተጻፈ እግዚ አብሔር ጥበብንና ዕውቀትን ከአይሁድ አርቆ ለእናንተ ሰጥቶአ ችኋልና ::

፵፫፤ስለዚህም ዲያብሎስ በተቀደ ሰች የእግዚአብሔር ቤተ ክርስቲ ያን ላይ ቀና በእናንተም ላይ ፍር ሃትንና እንቅጥቅጥን፣ ሕማምንና ጭንቅን፣ ጽርፈትንም ሁሉ አመ ጣባችሁ ::

፵፬፤ከወንጀለኞች መለየትም ይህ ነው፤ሰይጣን የአይሁድን ሕዝብ ክርስቶስን ይገድሉ ዘንድ ገዝቷ ቸዋልና።

፵፭፤እናንተ ግን ጠላችኋቸው፣ የሥራቸውንም ክፋት ናቃችሁ ስለዚህም በጻድቅ ኢዮብ ላይ እንዳደረገው ፈተናንና ጠብን በእናንተ ላይ አመጣ ::

፵፮፤ የኢዮሴዴቅ ልጅ ኢያሱ ንም እንደ ተቃረነው እኛንም ሰይጣን ብዙ ጊዜ እንደ አጃ ያንጠረጥረን፣ ሃይማኖታችንንም ያደ ክም ዘንድ ይወዳል ::

፲፱ ኢዩኤል.፪. ፳፰ ፤ የሐ ሥራ ፪. ፲፯
፳. ኢዮብ . ፪. ፯
፳፩. ዘካ፡ ፫..፩ . ፪
፳፪. ሉቃ ፳፪.. ፴፩

፴፫፤ ወባሕቱ እግዚእነ ይምህረነ ረገሞ ወገሠየ እንዘ ይብል ለያኅሥ ርከ እግዚአብሔር ዘአድንነነ ለእስ ራኤል እስመ ይቤ ቀዲሙ እንዘ ጉቡኣን አንትሙ ሰአልክዎ ለአብ በእንቲአክሙ ከመ ኢይድክም ሃይ ማኖትክሙ[፩፱] ::

፴፬፤ እስመ ኮነ ፍልጠት ወጋዕዝ እኩይ ማዕከለ ማኅበረ አይሁድ ወሰዱቃውያን እለ ኢየአምኑ ትን ሣኤ ሙታን ወፈሪሳውያን እለ ይብሉ ሶበ ተወልደ ብእሲ ይጽ ሐፍ ላዕሌሁ ኵሎ ዘይገብር ኀጢ አተ::

፴፭፤ወዘሂ ይከውን እሉኬ ኢየአምኑ ግብሮ ለእግዚአብሔር ላዕሌነ ወካ ዕበ ይብሉ ኢይትነሥኡ ሙታን በአሐቲ ሰዓት::

፴፮፤ወእሙንቱሰ ኢየአምኑ ትንሣኤ ወቦ ዕደው እለ ኢይጥዕሙ እክለ ዘእንበለ ያጥምቁ ኵሎ ጊዜ ዐራታተ ወኵሳኵሳተ ወአጽሕልተ ወጽዋዓተ ወምንባራተ የሐፅቡ ወያነጽሑ በማይ[፩፪]፤

፴፯፤ወቦ ካልኣን እለ ይሰመዩ ፍዮ ኒዮክን እለ ይኄልዩ ወይብሉ ከመ ወልደ እግዚአብሔር ብእሲ ውእቱ ወተወልደ በፍትወተ ሥጋ በሩካቤ ዮሴፍ ወማርያም እንዘ ንጹሓን እሙንቱ እምዘ ከመዝ ግብር::

፴፰፤ነገር ግን ጌታችን ያስተም ረናል፣ እኛን እስራኤልን ያዳነን እግዚአብሔር ያዋርድህ ይገሥ ጽህ ብሎ ረገመው ገሠፀውም፤ እናንተ ቀድሞ ተሰብስባችሁ ሳላ ችሁ ሃይማኖታችሁ እንዳይደ ክም ስለናንተ አብን ለመንኩት ብሏልና ::

፴፱፤በአይሁድ ማኅበር የሙታ ንን መነሣት በማያምኑ በሰዱቃ ውያንና ሰው በተወለደ ጊዜ የሚሠራው ኃጢአት ሁሉ የሚ ሆነውም በእርሱ ላይ ይጻፋል በሚሉ ፈሪሳውያን መካከል ክፉ ክፉ ክርክርና መለያየት ተደር ጓልና::

፵፫፤እሊህም በኛ ላይ የእግዚ አብሔርን ሥራ አያምኑም፤ ሁለተኛም ሙታን ባንዲት ሰዓት አይነሡም ይላሉ ::

፵፮፤እሊህ ግን የእርሱን ትን ሣኤ አያምኑም፤ ሁለጊዜ አልጋ ዎችንና ቍሳቁሶችን ሳያጠምቁ የፃሕሎችንና ጽዋዎችን መቀመ ጫዎችንም ሳያጠምቁ በውሃ ሳያ ጥቡና ሳያጠሩ እህልን የማይቀ ምሱ አሉ::

፵፯፤ እንደዚህ ካለ ሥራ ንጹ ሐን ሲሆኑ የእግዚአብሔር አብ ልጅ ወልድ በማርያምና በዮሴፍ ሩካቤ በሥጋ ፈቃድ የተወለደ ሰው ነው ብለው የሚያስቡ ፍዮ ኒዮክን የሚባሉ ሌሎች መናፍ ቃንም አሉ ::

፵፪ ሉቃ. ፳፪. ፴፩. ፴፪
፵፫. ማር. ፯. . ፫. ፱

፴፮፤እሱኬ እለ እምትካት የዐቅቡ ሕገ አበዊሆሙ ::

አንቀጽ ፴ወ፪

በእንተ ዘከመ አብአ ሰይጣን ፍል ጠተ ወጋዕዘ ውስተ ቤተ ክርስቲ ያን በከመ ገብረ ቀዲሙ ላዕለ ሕዝበ እስራኤል ::

፩፤ናሁኬ ርእዩ ወሰብዉ ኪኖ ወምግ ባሮ ለሰይጣን ጸላኤ ኵሉ ሠናያት ዘከመ ይገብር ፍልጠተ ወኑፋቄ ወዕልወተ ማእከለ አሕዛብ::

፪፤ቀዳሚ ፍልጠት ዘገብረ ሞስለ ሲሞን በሀገር እንተ ጎቶን ::

፫፤ ወውእቱሰ ብእሲ መሠርይ በኪነ ርእሱ ርኩስ ለብሶ ለሰይጣን ከመ ልብስ ወተቀንየ ለ*ቱ ከመ ገብር እንዘ ኵሉ እኵየ ፈቃደ ይገ ብር[፩]::

፬፤ወፈልጾስ ወንጌላዊ እጉነ ገብረ ጎይለ ወተአምራተ ዐበይተ ወፈ ወሰ ዱያነ በሀገረ ሰማርያ በጸጋ እግዚአብሔር ወበትእምርተ መን ፈስ ቅዱስ::

፭፤ወርእዮሙ ሰብአ ሰማርያ ኵሉ ምግባሮ ጸንዑ በሃይማኖቶሙ ወአ ምኑ በእግዚአብሔር ወተጠምቁ በስመ ኢየሱስ ክርስቶስ ::

፴፯፤ እሊህም ከቀድሞ ጀምሮ የአባቶቻቸውን ሥርዓት ይጠብ ቃሉ::

ሠላሳ ሁለተኛ አንቀጽ

ሰይጣን ቀድሞ በእስራኤል ላይ እንዳደረገው በቤተ ክርስቲያን ውስጥ ክርክርንና መለያየትን እንዳስገባ ይናገራል::

፩፤ እነሆ መለያየትንና ጥርጥ ርን መወንጀልንም በሕዝብ መካ ከል እንደሚያደርግ በጐዎች ሥራ ዎችን ሁሉ የሚጠላ የሰይጣንን ተንኰልና ሥራ እዩ አስተውሉ ::

፪፤ስሚ ጎቶን በምትባል አገር ላይ ከሲሞን ጋራ ያደረገው መለያየት መጀመሪያ ነው ::

፫፤ ይህ ሥራየኛ ሰው በረከሰ በራሱ ተንኰል ሰይጣንን እንደ ልብስ ለበሰው፤ ክፉ ፈቃድንም ሁሉ እየሠራ እንደ ባሪያ ተገዛ ለት::

፬፤ወንድማችን ወንጌላዊው ፊል ጶስም ጎይልንና ታላላቆች ታም ራትን አደረገ፤ በእግዚአብሔር ጸጋና በመንፈስ ቅዱስ ምልክት ነት በሰማርያ ሀገር ድውያንን ፈወሰ::

፭፤የሰማርያ ሰዎችም ሥራውን ሁሉ አይተው በሃይማኖታቸው ጸኑ፤ በእግዚአብሔርም አመኑ፤ በኢየሱስ ክርስቶስ ስምም ተጠ መቁ::

፩. ግብ ሐዋ. ፰. ፱ ፲፩